# <u>ውሀ የገባ አሞሌ</u>

## <u>(ለዶክተር ያዕቆብና መሰሎቻቸው መልስ ብጤ)</u>

ከ --ሰንደቁ ዘላላም

የሀገራችን አዛውንት ሲተርቱ ዕድሜ ያልመከረው ሽማግሌ ውሀ እንደገባ አሞሌ ነው ይላሉ:: ይሟሟል:: ዶክተር ያዕቆብ ባለፈው ሰሞን በሰጡት መግለጫ/ቃለ መጠይቅ የብዙ ድርጅቶችን መሪዎች፤ ለለውጥ የታገለውን ትወልድ ሁሉ አውግዘው መናገሩ ቀርቶባቸው በቃኝ አበቃሁ ማለት ሲችሉ የራሳቸውን ምፀት በሌሎች ላይ ሁሉ ለመጫን ጥረው በመገኘታቸው የፈነደቀው የወያኔ ጎራ በዚህ በዚያ አጆሀ አጆሀ እያላቸው ነው:: ሰውየው ዳግም ሟሙ:: መርስዔ ኪዳን በተባለ ወያኔ የተፃፈውንና በወያኔ ድረገፅ በአይጋ ፎረም የተፃፈውን ያነቧል::

ዶክተር ያዕቆብ የንጉሱን መንግሥትና ስርዓት የታገለውን ትውልድ ሁሉ በአክራሪነት፤ ባለመቻ ቻል ና በሌላ ሌላም ሁለ ይወነጅላሉ:: ግራ ክንፍ ወይም ማርክሲስት ሌኒኒስት የነበሩ ይመስልም በዚህ ርዕዮት ላይም የጭቃ ጅራፋቸውን አውርደዋል:: የዚያ ትወልድ አባላት አሁንም በየድርጅ ቱ አሉና ሁሉም ወርደው ሃላፊነቱ ለአዲስ ትውልድ ይሰጥ በሚልም እነሆ እኔ በበኩሌ ከቦታዬ ለቀቅኩ ይላሉ ::በዘመነ ኒክሰን “ ውሄን ዘ ጎይንግ ጌትስ ታፍ ዘ ታፍ ጌት ጎይንግ” የተባለውን ያስታውሳል:: ጉዞው ሲከብድ ብልጦች ሸብረክ--ላጥ ይላሉ ዓይነት ነው:: የወይዘሪት ብርቱካን ፓርቲ መሪ ነኝ ብለው ከርመው የታሰረችው መሪ ሳትፈታ ከቦታዬ ወርጃለሁ ማለቱ የእኚህን ሰው የቆየ ትችት ጋባዥ ጠባይ የሚያሳይ ነው ቢባል ትክክል ነው:: ዶክተር ያዕቆብ በትግሉ ዙሪያ ለረጅም ጊዜ መኖራቸው በደፈናው ባያከራክርም ሚናና ቦታቸው ግን በግልፅ መቀመጥ ያለበት ነው:: ከዋለልኝ መኮንን ጋር በአይሮፕላን ጠለፋ ተካፍላ ሌሎቹ በግፍ ሲገደሉ የተረፈች ውን ዜጋ ለመከላከል በጥብቅና መቆማቸው ዛሬም የሚያስመስግናቸው ነው:: ከዚያም በኢሕአፓ አባል ሆነው በዚያውም ወደ ኬንያ ተሰደው በዚህ ቦታ ለድርጅቱ ለአጭር ጊዜ መስራታቸው ይነገራል:: ከኬንያ ወደ አሜሪካ ድርጅቱን ትተው ከሄዱ በኋላ ግን ከኢሕአፓ ጋር የነበራቸው ቀጭን ግንኙነት ተበጥሷል:: ዶክተር ያዕቆብ በኢሕአፓ በነበሩበትም ጊዜ በግራ ርዕዮት ያመኑ ናቸው ማለት የሚቻል አልነበረም ሲሉ የሚያውቋቸው ብዙ ጊዜ ተናግረዋል:: የኢሕአፓ ያመራ ር ኮሚቴዎች አባል እንዳልነበሩ ውስጠ አዋቂዎች ከዓመታት በፊት ገልፀውታል:: በነበረው ጎር ፍ ተጠርገው የዚህ ድርጅት የአጭር ጊዜ አባል ሆኑ እንጂ ዶክተር ያዕቆብ በዚያ ትወልድ እንቅ ስቃሴ ቦግ ያለ ሚና ሆነ የአመራር ቦታ የያዙ አልነበሩም:: በዚያን ጊዜ ግራ ቀኙ ኢሕአፓ ነበር ና ዶክተር ያዕቆብ የዚህን ድርጅት መሰረታዊ እምነት ከልባቸው ባያስቀምጡም አባል ነበሩ::

ወደ አሜሪካ ዘልቀው ትምህርታቸውን ቀጥለው ኑሮአቸውን ሲያደላድሉ ኢሕአፓ ግን መራራ ትግሉን ቀጥሎ ነበር:: ከዚያም ውሎ አድሮ ዶክተር ያዕቆብ በፖለቲካው መድረክ ብቅ ያሉት ደርግ ሊወድቅ ሲልና ህብረት ለመመስረት ጥረት ተደርጎ በቶሮንቶ ካናዳ ስብሰባ ሲደረግ ነው:: ይህ ስብሰባ የተቃዋሚዎችን ህብረት እንዳያቋቁም ኃያሉ መንግሰትና ቅጥረኞቹ ባከሄዱት ሻጥር

ዶክተር ያዕቆብ፣ ዛሬም የፀረ ሕዝብ ሻጥር ተካፋይ የሆኑት ኤፍሬም ይስሓቅ፣ሚቹ ደረጃ ዴሬሳና የዚሁ ሰው ተቀጣሪ የነበረው ሌላ ስም አይጠሬ ምሁር፣ ወዘተ ተካፋይ ሆነው የቶሮንቶውን ስብሰ ባ ማኮላሸት ብቻ ሳይሆን ቀጣይ ቀጠሮውም በጊዜ እንዳይሳካ አድርገው ብዙ ጉዳት አድርሰዋል:: ዶክተር ያዕቆብ የብሄረሰብ ድርጅቶችን ለማሰማማት ብዙ መድከማቸውን ወያኔው መርስዔም በአድናቆት ነግሮናል:: ወያኔ ለስልጣን ሲደርስም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በወያኔ ዙሪያ መታየታቸውና ውሎ አድሮም በዶሮ እርባታ ንግድ መግባታቸውና ከዚያም ቅንጅት በተባለው ሰብስብ ውስጥ አመራር ኮሚቴ አባል ሆነው መድረክ መውጣታቸው ታይቷል::ዶክተር ያዕቆብ በአሜሪካ ቤተሰብ መስርተው በህግ አስተማሪነትና በህግ አማካሪነትም ደረጃ ሲሰሩ መቆየታቸው ም የሚታወቅ ነው:: የቅንጅት ውስጥ አወቆች ዶክተር ያዕቆብ ለወያኔ ጎብደድ በማለት ቅንጅት ን ካልፈሰፈሱት ምሁሮች አንዱ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ::

ወደ ዶክተር ያዕቆብ ኑዛዜ አይሉት ክስ ከመግባታችን በፊት ግን ማተብ በጣሾችን በተመለከተ በአጭሩም ቢሆን መተቸት እንገደዳለን:: የግራ ክንፍ ድርጅቶችና ኮሙኒስት ፓርቲዎች አባል ነበርን ብለው ከዚያም ክደው ተቀይረው የለየላቸው ፀረ ኮሙኒስት የሆኑ ብዙዎችን ታሪክ ስንመ ረምር ከፅንፍ ፅንፍ መሆኑን እንረዳለን::ቆብ የቀደደ ቄስ እንዲሉ ነው:: ጭፍን ማኦኢስት ነን ብለው ቧርቀው የከረሩ ጸንጫዎችየሆኑት ዝርዝር ጥቂት አይደለም:: ክህደቱ የተባለው የወያኔ ቡችላ ለምሳሌ በየሁኔታው አቅዋምን መቀያየር የፖለቲካ ብስለት ነው ሲል በሰሞኑ ፅፏል:: ግትርነትን መቋቋም በሚል ሽፋን  አድርባይነትንና አቅዋመ ቢስነትን ማንገስ መሆኑ ነው:: የአፄ ኃይለሥላሴን ስርዓት  ለመጣል በተደረገው ትግል ጭራሹኑ ያልተሳተፉና በፀረ ደርጉም ትግል ጥግ ይዘው ተመልካች የሆኑ ዛሬ አዲስ ታሪክ ሊፅፉ በመነሳት ያን የታገለውን ትውልድ መቀጥ ቀጥ ልምዳቸው ሆኖ ይገኛል:: ዛሬ የፖለቲካ ድርጅቶች ኮከቦች ነን ሊሉ የተነሱ ብዙዎች የትግ ል ታሪካቸው ዜሮ ካልነበር አሳፋሪ ይዘት የነበረው መሆኑን ስንጠቅስ ስም ጥሩ ብሎ የሚያሰቸግ ረን ሰው የሚኖር አይመስለንም:: ሠያ ትውልድ ማተብና እምነት ነበረውና ይህ ፅናት ሆነም እም ነት የሌላቸው ያን ትውልድ በግትርነትና በአክራሪነት ለመክሰስ ይጮኻሉ:: ዶክተር ያዕቆብ ለዚህ መሰል ሽንጌዎች አጃቢ ናቸው:: ያ ትውልድ ግራ ከንፍ ስለነበር መቻቻልን አይወድም ነበር ፣ ተናክሶ ተጨራረሰ ብለው የደርጎችን የወንጀል መሸፈኛ ልፈፋ የራሳቸው አድርገው ይቀርባሉ: : ማተባቸውን የበጠሱ ወይም ሰልፋቸውን የቀየሩ፣ ትላንት ለጭቁኖች ቆምን ብለው ዛሬ ለበዝባ ዦች የሚቆሙ ወይም በዝባዥ ይሆኑ፣ ትላንት ለሕዝብ አንድነት እንሰየፋለን ሲሉ ተደምጠው ዛሬ በአሳፋሪ መንገድ ወድ ጎጣቸውና ብሄረሰባቸው ተመልሰው ዘረኞችን ሲያጅቡ የእነዚህ ሰዎች አንጎል የታመሰ ባህር መሆኑ የሚጠበቅ ነው:: ስነ ልቦናቸውና የቀራቸው ህሊና ይናጣል:: ከዳህ ከዳሽ ቃጭል በውስጣቸው  ያቃጭልባቸዋል:: ከአፈርኩ አይመልሰኝ ይመጣና ያደቆናቸውን የክህደት ሰይጣን ጋልበን ብለው ይጎነበሱለታል:: እሱም ይጋልባቸውና ዛር እንደያዘው ሰው የቅሌት ቋንቋኛን ያስለፈልፋቸዋል:: በፖለቲካው መስክ የወሊሶው አባ ወልደ ተንሳይ ማስፈለጋ ቸው ይታያል!

የዶክተር ያዕቆብ በዚያ ትውልድ ላይ መዝመት ለወያኔ ያስደሰተው (በለሆሳስ ነካ ቢያደርጉትም) የተቃዋሚ ድርጅቶችን መዳከምና በተወሰነ ደረጃ መፍረስን በዋና ደረጃ በታጋይ ድርጅቶች አባል በነበሩ ግለሰቦች ምክንያት የመጣ ነው ብሎ ስለሚደመድም ነው:: እኔም ኢሕአፓ ነበርኩ፣ እገሌም መኢሶን ነበር፣ ሌላውም ሌላ ሌላ ብለው የነበርንባቸው ድርጅቶች ልምድ ተፅዕኖ አሁን ያለንበትን ድርጅት ጎዳውና ለወጣቶች መልቀቅ አለብን ይላሉ:: ዶክተር ያዕቆብ በሚገባ ሊጨብጡት ባልቻሉት ፖለቲካ ገብተው ከያኔ እስከዛሬ ሲያደፈርሱ የነበረውን በቃ ብለው መተዋቸውና ወደ ትርፍ አስገኚ የዶሮ እርባታው ማተኮራቸው እሰየው የሚያሰኝ ነው:: ሌሎች መሰሎቻቸውም ቢከተሉ ይመረጣል:: የፖለቲካ እውቀትና ልምድን በደፈናው ለወጣት መልቀቅ በሚል መዳፈኑም ብልህነት አይደለም:: ክህደቱም አንፃራዊ ወጣትነት ያሳይ የለ? ዶክተሩ ግን ኢሕአፓንም፣ መኢሶንንም፥ የአልባኒያና ስታሊን አምላኪውን ወያኔ ማሌሊትንም፣ የሶቭየት ታዛዦን ኢሠፓንም በአንድ ርዕዮትና ልምድ ቋት ከተው ማቅረባቸው ስህተት ከመሆኑ ሌላ ያስገምታቸዋል:: ዛሬ አለምንም የረባ የፖለቲካ አቅዋም ወይም ርዕዮት ልዩነት እርስ በርሱ የተናከስ ተቃዋሚ ስብስብ አባል ሆነው የቆዩት ዶክተር ያዕቆብ በጠራ የፖለቲካ አቅዋም ልዩነት የተለያዩትን እነ ኢሕአፓመ መኢሶንን ለምሳሌ በአለመቻቻል ለመክሰስ መነሳታቸው ያስገርማል:: ኢሕአፓና መኢሶን በአብዮቱ አካሄድ፣ በአደረጃጀት፣ ስልጣን ከያዘው ጋር በማበርና ባለማበር፣ በትግል ስልት ወዘተ መሰረታዊና ሊታረቅ የማይችል ልዩነት ስለነበራቸው ሳይተባበሩና ወይም እንደሚባለው ሳይቻቻሉ ቀርተዋል:: ዶክተር ያዕቆብ እስቲ መለስ ብለው የቅንጅት ሂደት ይዘቱን ያጢኑ! መሪያቸውን አሳስረው በአልባሌ ምክንያቶችና እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በሚል የምሁር ግብዝነት ለክፍፍል የበቁ ሆነው ሳለ በምን የሞራል ብቃት ነው ታዲያ ያን ትውልድ ሊከሱ የሚነሱት?ያ ትውልድ ርዕዮትና የጠራ የፖለቲካ አቅዋም ስለነበረው የሀሳብ ልዩነቶች በሀሳብ መፋጨትና ክርክር ሲስተናገዱ (የቀድሞ የተማሪ ማህበራት ትግልና ጉባዔዎች ምሳሌ ናቸው) የሚሰነዘሩ ቅፅሎች ስድብ የሚመስሉት ለክቡር ዶክተሩና ለፖለቲካ አላዋቂዎች ነው:: የወያኔ ቅጥረኛ ብሎ መጥራት በመጀመሪያ ደረጃ የግለሰቡን ማንነት ገላጭ ነው::አንድ ግለሰብ ከሀዲ ሲባል፣ባንዳ ሲባል፣ ሆዳም ሲባል ዘለፋ ሳይሆን አቅዋሙን መግለጥ ነው:: ስሙ ሳይሆን የከረፋው፣ ጠሪውም ሳይሆን ያጠፋው የግሰለሰቡ አሳፋሪ አቅዋም ነው ተጠያቂ:: ባንዳን ባንዳ ይሉታል እንጂ ማንዴላ ብለው ያቆላምጡታል ታዲያ? አይበቃም! ስለዚህም ያ ትውልድ መቻቻልን አያውቅም ነበር፣ ዴሞክራሲን ተፃሮ ነበር፣ አክራሪ ነበር፣ ወዘተ በሚል ሀቅን አጣሞ ታሪክን በጠራራ ፀሐይ ማጅራት መምታቱ ቢያበቃ መልካም ይሆናል::

ሀገርን በተመለከተ፣፥ ወያኔን ጠላት ብሎ መታገልን በተመለከተ የዶክተር ያዕቆብ አቅዋም አጠያያቂ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል:: የወያኔ አገዛዝ ይውደም ሕዝባዊ ጩኸት ጆሮአቸውን ያማቸዋል:: በወያኔ ላይ ማክረር ስህተት ነው ባይ ናቸው:: አይ ያ ትውልድ ብለው ያማርራሉ:: የእሳቸው የሰለጠነ ፖለቲካ ለወያኔ ጎንበስ ለስለስ ማለትና ለምዕራባውያን ታዛዥ መሆን ነው::

ይኼ ታዲያ አልዋጥ ቢለን፣ እንደ ጀግናው ማቹ ፕሮፌሰር አሥራት ይህ ሁሉ የሆዳሞች ፖለቲ ካ ነው ብንል፣ የፈሪዎች አቅዋም ነው ብንል ምን አጠፋን? ዶክተር ያዕቆብ በመደብም ሆነ በፓለቲካ እምነታቸው ከሕዝብ ጎራ መውጣታቸውን እስካዛሬ ካላወቁ እነሆ መርዶውን እንንገራ ቸው:: ሁኔታው ሲከብድ ያውም የታሰረችው የድርጅታቸው መሪ ሳትፈታ በቃኝ ብሎ ሰበብ ደርድሮ ዞር ማለት ያስወቅሳል እንጂ የሚያስመሰግን ድርጊት አይደለም:: ተቃዋሚ ድርጅቶች አሁን ባሉበት የተዳከመ ደረጃ የደረሱት <u>መጀመሪያ በወያኔ አፈናና አፍራሽ ድርጊት የተነሳ ነው::</u> ይህንን ለመሸፋፈን ዶክተሩ መነሳታቸው በጣም ያሳዝናል:: ቅንጅትና ህብረት ወያኔን በ1997 ኡ ምርጫ አሸንፈውታል:: የወያኔ ቡድን ሀይልን ተጠቅሞ የሕዝብን ድምፅ ሲሰርቅና ሲያፍን ምዕራባውያን ደግሞ ጥቅማቸውን ያስቀደሙ መሪዎችን ደልለውና አስፈራርተ ው የሕዝብን ትግልን አድማ መቅበራቸውን ገና አልረሳንም:: ቅንጅትን ለማፍረስ በወያኔ ትዕዛዝ ስር የሚንቀሳቀሱ ሰርጎ ገቦች የፈፀሙትን ደባ ሕዝብ ያውቃል፣ከሀዲዎችም ለታሪክ ፍርድ ተመዝግበዋል:: የድርጅት መሪዎች ለሚፈፅሙት ስህተት ተጠያቂ መሆናቸው ባይቀርም ለደረሰ ው ቀውስ ግን በዋናነት ተጠያቂ ወያኔ መሆኑ ሳይነሳ የተወሰኑ ግለሰቦችን በማንሳትና የነዚህንም የቀድሞ የድርጅት ቱሪስትነት ፈጣን ጉዞን በማውሳት ያን ትወልድ በእጅ አዙር ለመወንጀል መነሳቱ የሚያዋጣ አይደለም:: ዶክተር ያዕቆብ መሸከም የሚገደዱት ከባድ መስቀ ል አለና ይህንን ራሳቸው በጫንቃቸው ይሸከሙ እንጂ ታሪክን በመከለስ እንደገና ለወያኔ ታዳጊና ረዳት ባይሆኑ ይሻላቸዋል::

ዕድሜ ፀጋ ነው፣ቁም ነገር ከሰሩበት፣ ትምህርት ከገበዩበት:: ኩኩሉ ዶክተር!